# ይድረስ ለተነሳሂው ወገኔ

**ሰከን በል !**

የሙዚቀኛ ይሁኔ በላይ ጠንከር ያለ መልክት ያላትን ከጊዜው ጋር በሰላም የተወለደች ሙዚቃ ወደድኩለት ።
አሁን የሃገራችን የፖለቲካ ጀልባ ከወጀቡ ጋር እልህ የተጋባ ይመስላል በርግጥ አቀዛዘፉም ከዚህ የሚያድነው እልነበረም።
ከመቼውም ይበልጥ ዛሬ በሰከነ አእምሮ ማሰብና በረጋ ልቦና ማስተዋል የሚያስፈልግበት ደረጃ ላይ ደርሰናል ።
ኢትዮጵያ ሃገራችንን በቸርነት ለማቆየት የቀድሞውን አንድነት መቻቻልና ሰላማዊ ህይወት ቀጥለን ማየት የምንመኝ ሁሉ ያንን የቀደመው ባህላችን የሚፈቅደውን አክብሮትና አንድነት አሁንም ልንጠቀምበት ይገባናል ።
ዛሬ ሃገራችን በጥቂት ጎሰኞች እጅ ወድቃ ህዝቧ መኖር ያቃተበት ደረጃ ላይ ብንገኝም ጨርሶ ከመጥፋት ግን ራሳችንን በራሳችን መታደግ እንደሚኖርብን ማንም ሊነግረን ወይንም ሊያስረዳን አይገባም ።
ወደ ጨርሶ መጥፋት አልያም መከፋፈል የሚወስደው መንገድ ጠባብ ቢሆንም መንገዱ መኖሩ በራሱ ደግሞ ቀላል ችግር መስሎ ሊታይ አይችልም ።
የኢህአዴግ መንግስት በአሁን ሰዓት ወደ ዕርቅ አልያም ወደ ድርድር ለመሄድ እንኳንስ ሃሳብ ህልምም ያለው እያልመሰለን መጥቷል ይህ ደግሞ የችግሩን መባባስ የሚያመላክት ሁኔታ መኖሩን በሚገባ ያሳየናል።
በብሄራት በኩል ደግሞ የእልህ ሁኔታዎች ጎላ ጎላ እያሉ መታየት ጀምረዋል እነዚህን ሁለት ችግሮች ማስታረቅና ማቻቻል የምንችለው በትክክለኛ አመጽና በአንድነትን የመቆም ጽናት ብቻ ነው ።
አመጽንም ሆነ ተቃውሞን ማድረግ የምንችለው በአንድነት ስንቆም ብቻ እንጂ እዛችና እዚች በምንለኳኩፋት ሁኔታዎች ውስጥ በሚፈጠሩ አለመግባባቶች በሚፈጥሩት ክፍተት ውስጥ መሆን የለበትም ።
ዛሬ እርስ በርሳችን የምንነቃቀፍበት ጊዜ ላይ አይደለንም ይልቁንም በልዩነታችን አንድነታችንን አጥብቀን ማመን ይኖርብናል።
በሃገራችን ውስጥ ባለው የድርሻ ፖለቲካ ወይንም የውርስ ፖለቲካ አማካኝነት የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ፤ የኢትዮጵያ አየር መንገድ፤ የኢትዮጵያ ቴሌኮሙኒኬሽን፤የአዲስ አበባው ቀዳማዊ ሀይለስላሴ ዩኒቨርሲቲ፤ የኢትዮጵያ ብሄራዊ ጦር: እንዲሁም ታላላቅና ግዙፍ የንግድ ማዕከላት ወዘተርፈ ከጫፍ እስከ ገደፉ በአንድ ብሄር ሰዎች ከተሞሉ ዘመን ቆጥረናል ።
በምድራችን ፍትህ ተዛብቷል፤ ንግድና ንዱስትሪ የፓርቲ ሃብት ከሆኑ ዓመታት አልፈዋል ።
መልካም አስተዳደር እየተባለ ስም የሚሠጠው ጉዳይ ሃገሪቱን ከየትም ወደየትም ማንቀሳቀስ ካለመቻሉም በላይ ተራውና ድሃው ህዝብ በምንም አይነት ሁኔታ ማንኛውንም ጉዳይ ሊፈጽም የማይችልበት ደረጃ ላይ ደርሷል።
መብትና ግዴታ ምን እና ምን እንደሆኑ አይታወቅም ::
አንድ የኢህአዴግ ተራ ወታደር ወይንም የትልልቅ ተቋሞች የጥበቃ ስራ ላይ የተመደቡ የወያኔ ዘበኞች የፓርቲ አባል ካልሆኑ ትልልቅ ባለስልጣናት የላቀ መብት አላቸው ::
ቀድሞ ቀላል ጉቦ መስጠት የሚታወቀው ለትራፊክና ለቀበሌ ሊቀመንበር አልፎ አልፎም በፍርድቤት አካባቢ እንደነበረ የምናውቀው ዛሬ ዛሬ ጎንበስ ብሎ የወደቀን ለማንሳት ጉቦ ካልሰጡ ቀና ማለት አይቻልም :: ጉቦ የሁሉም ቢሮዎች የስራ ማስፈጸሚያ ህጋዊ አሰራር ሆኗል።

ዳሩ ይሄ ችግር ደግሞ በገዢው ብሄር ብቻ የሚፈጸምም አይደለም  ፈቃዳቸው ሆኖ በሃገሪቱ ባሉ ክልሎች ውስጥም የባሰና ህዝቡን መላወሻ ያሳጣ ጉዳይ ነው  ።

በዚህም ላይ እስራት ከስራ መታገድ መግቢያ መውጫ ማጣት ብሎም እፈናና የገቡበት መጥፋት የዕለት ተዕለት ኑሯችን ሆኗል

አሁን የኢህአዴግን መላ ማጣትና ብልሹነት ለመናገር ፈልጌ ብቻ አይደለም ከዚህም በኋላ ስለ ወያኔዎች አሰራር ማውራት ፈልጌም እይደለም ችግሩን ሳናውቅ ወደመፍትሄ መሮጥ የማንደርስበት ጉዳይ ሆኖብን እንዳይቀር ለማሳሰብ ነው።

ችግሩን በሚገባ ያወቀ ሰው  መፍትሄውንም በሚገባ ማወቅ እንዳለበት ለማሳሰብና በተለይም ዳያስፖራውን ሰከን በል ለማለት ፈልጌ ነው  ::

እዚያ እርስ በርሳችሁ ሥጋጃ የምትነጣጠፉት ፡ ትላልቅ ሽልማቶችን የምትሰጣጡት ዲያስፖራዎች ( ቀድሞ ማመስገን ለኋላ ሃሜት ይቸግራል ) እንዲሉ ከመሆን የሚዘል አንድም ነገር አይኖርም ።

ታዋቂው አለማቀፍ የስፖርት ሰው ሌሊሳ ዲሳሳ ማንም ሰው ሊማርበት የሚገባ ንግግር ተናግሯል ( የኢትዮጵያዊነቴን...... የድርሻዬን ተወጣሁ እንጂ እኔ ጀግና አይደለሁም ) አባባሉ ጀግንነት ያለበት ነው ::

በአሜሪካ ግን ተቃዋሚነት ጀግንነት ሊሆን የሚችልበት ሁኔታ ሊገባኝ አይችልም ምናልባትም ራሳችሁ በራሳችሁ ተጀጋግናችሁ ስታበቁ ልክ እንደኮሪያ ዘማቾች ኒሻን ለኛም ካልተሸለምን ብላችሁ እንጂ ኢህአዴግ የቱንም ያህል ግዙፍ ቢሆንና እሱን መቃወም ጀግንነት ሊሆን አይችልም::  አለበለዚያ ጀግና ማለት ትርጉሙ እናንተ የምትሸላለሙበት ደረሰኝ መቀባበያ አይደለም::

አጋጣሚ እግኝቶ አልያም ቪዛ ተሳክቶለት ወይንም ደግሞ በህዝብና በሃገር ወዝ ወደ ውጪ ተልኮ በዚያው የሸመጠጠውንና እንደምንም አሜሪካ የገባውን  ጀግና ስትሉ የአንድ ሰሞን ወሬያችሁ ታደርጉታላችሁ.......  እዚህ ያለውንና ፊት ለፊት ችግሩን ከህዝቡ ጋር የሚጋፈጠውን : ችሎታውን እና ሞያውን ለወገኑ የሚያካፍለውን : እንዲሁም ህዝቡንና ሃገሩን የሚያገለግለውን ደግሞ ሆዳም ትሉታላችሁ  ... ይሄ ነው የዳያስፖራው ፖለቲካ ???  ይሄ ነው የናንተ እውቀት ??

ጎበዝና ፈሪ ትርጉሙ የጠፋበት ትውልድ እንዳናስከትል ሰከን በሉና አስቡ ጎበዝ

እንግሊዞች አጋር መስለው ሲያበቁ የሃገራችንን ሃብት ሲዘርፉ የሰማ ጀግናው በቀለ ወያ ከመሃል ተነስቶ ወደ ደቡብ ወርዶ ድባቅ የመታቸው ነው ጀግና !!!

ከሰሜን ተነስቶ ምስራቅ ላይ የሃገሩን ጠላት ድል የነሳው ነው ጀግና ....... አሉላ አባነጋና አብዲሳ አጋ ናቸው ጀግና ፤በላይ ዘለቀና አባነፍሶ ናቸው ጀግና ......................አታናዱና !!!

የአሜሪካ ጀግኖች እባካችሁ ሰከን በሉ !!

መቼም ከናንተ በላይ በአንድ ለመሆን ፤ ሁሉን ለማስተባበርና ሠልፍ ለመጥራት፤ ውይይቶችን ለማካሄድ ፤ ፓምፕሌቶችን ለማዘጋጀት፤ እውነቱን እና ጭብጡን ለህዝባችን ለማሳየትና ለመናገር፤ ምሁራኑን እና ሽማግሌውን ለማማከርና ሃሳብ ለመለዋወጥ ወ.ዘ.ተርፈ ከናንተ በላይ እድሉ ያለው የለም::

ይህ ሊያመልጣችሁ የማይችል የዛሬው ምኞቴ ሲሆን ተናጋሪውን ሁሉ ጀግና ተቃዋሚውንም ታጋዩንም ሁሉንም  ጀግና ማለት ተገቢ ሆኖ አላገኘሁትም።

ሠውን ከችሎታውና ከሞያው በላይ ማወደስ ባሳለፍናቸው ብዙ ዓመታት ውጤቶቻቸውን ተመልክተናልና ለሁሉም እንደየ ችሎታው እንጂ ከሃገራዊ ግዴታው የበለጠ ስም መስጠት ለኋላ እንዳይመች ይሆናልና ሰከን በሉ !!

ዛሬ እርስ በርሳችን የምንነቃቀፍበት ጊዜ ላይ አይደለንም ይልቁንም በልዩነታችን አንድነታችንን አጥብቀን ማመን ይኖርብናል።

በፈረንጅ ሃገር የበለጠ ለዴሞክራሲው ቅርብ በመሆናችሁ በመማራችሁና በነጻነታችሁ ምክንያት ልዩነቶችን በመቀበል ማጥበብ ሲቻል የእርስበርስ አጉል መሞጋገስ  በጉልህ ይታያል ።

ማንም ሰው ማንኛውንም አይነት መርህ መከተል የማንኛውም ፓርቲ ደጋፊ ወይንም አባል መሆን ወይንም ደግሞ የማንኛውም ፓርቲ ደጋፊ ያለመሆን ሙብቱን ያላከበረ ሰው የራሱም አመለካከት ሊከበርለት ከቶም አይችልም ዴሞክራሲያዊነትም አይደለም::
መከባበርና መቻቻል ደግሞ ከነዚህ አመለካከቶች ይወለዳሉ።
በኢትዮጵያ አንድነት ያመነ ሁሉ ሊከበር ይገባዋል !
ማንም ምንም ሊያደርጋችሁ በማይችልበት ቦታ ሆናችሁ እንደልባችሁ ስለተናገራችሁ ጀግና የምትባሉበት ምክንያት ምንድር ነው ?
ኧረ ኀበዝ ሰከን በሉ !
ይሄ የኔ ፓርቲ ብቻ ነው የኢትዮጵያ ተድላ መሆን የሚችለው ! የኛ አመለካከት ብቻ ነው የሃገራችን መፍትሄ የሚሆነው ! የሚል አመለካከት ካሁኑ ካልተወገደ በስተቀር የኢህአዴግን ሰነፍ የፖለቲካ አካሄድ መቀልበስ አይቻልም።
ዴሞክራሲ የምንለውስ ይህንንው አይደለም ?
ሁሉም ግንቦት ሰባት ሁሉም ሰማያዊ ፓርቲ መሆን የለበትም ሁለቱም ፓርቲዎች ግባቸው አንድ እስከሆነ ድረስ ስለ ውስጣዊ አሰራራቸው ልዩነት እኛም ልንለያይ አይገባም።
አንድ ሰው የኢህአዴግ አባል ቢሆንም በትክክል መነጋገር መወያየት እስከቻለ ድረስ ልናከብረውና ለውይይት ልንጋብዘው ይገባናል ::
በሃገራችን ፓርቲ ለፓርቲ ለዘመናት ደም ሲፈስና ሃገር ሲፈርስ ቆይቷል ይህ ሁኔታ ዛሬ መብቃት አለበት ብለን ካልተነሳን የቀሪውም ትውልድ ዕጣ ፈንታ ያው ሞትና ሽሽት ሊሆን ፈቅደናል ማለት ነው።
ለኢትዮጵያ ህዝብ ሠላም ለሃገሪቱ አንድነትና ተስፋ የምታስብ ኢትዮጵያዊ ሁሉ ሰከን በልና አስብ !
ወደ አንድነት እስካልመጣን ድረስ፡ እርስ በርሳችን እስካልተከባበርን ድረስ፡ በሰከነ አእምሮ ራሳችንን ለውይይት እስካላዘጋጀን ድረስ፡ በዚህ በተበጣጠሰ የተቃውሞ አካሄድ በኢትዮጵያችን ውስጥ የተሻለ ለውጥ ማምጣት አንችልም ።
ለመሆኑ አሜሪካን ሃገር ያለው ዴሞክራሲ የስድብ ዴሞክራሲ ብቻ ነው እንዴ ? የሶሺያል ድህረ ገጾች በሙሉ ማለት እስኪቻል ድረስ የሚያስተናግዱት ስድብና አጉል የሆነ ሞራል ብቻ ነው ::
ስድብ የሚወልደው ስድብን ብቻ ነው ንቀትም የሚፈጥረው ንቀትን ነው አጉል ሞራልም በመናናቅና በመሰዳደብ ደግሞ አንድነትንና ሰላምን ማምጣት ማሰብ ራሱ ከጅልነት ያለፈ ጅልነት ነው ..........ኧረ ኀበዝ ሰከን በሉ !!
ህዝብ በተቆጣና ተቃውሞ በተነሳ ቁጥር ሁሉ መሪዎቹና አንቀሳቃሾቹ እኛ ነን የምትሉ የአሜሪካ ዲያስፖራዎች ከስራችሁና ከችሎታችሁ በላይ አትጩሁ !
ለነ ታማኝ በየነ ቁርበት ከማንጠፍና ዶላር ከማዋጣት ይልቅ ሜዲያውን እገልግሉ
ኢሳትንም የችግርና የሰቆቃ ጣቢያ አታድርጉት የጥላቻና የቂም አድባር አታድርጉት ።
ይልቁንምን እድሉ አላችሁና እውነትን ብቻ ተናገሩበት ይህ ነው ነጻነት ማለት !   እዚህ በቂ ውሸት ስለምንሰማ ከፈረንጅ ሃገር ሌላ ውሸት አያስፈልገንም።
የብሄር ሥም እየተጠራ የሚሰደብ ስድብ የምንሰማው ሶሺያል ሜድያዎች ላይ ነው ፡ ይህ ደግሞ ለብሄረሰቦች ግጭት ዋንኛው መሳሪያ ነው ፡ ሃገራችን ያለችበት ሁኔታ ደግሞ ከላይ እንደጠቀስኩት አደገኛ ሁኔታ ላይ ነው ፡ (የኢትዮጵያ ጠላቶችም ይህንን ከማድረግ እንደማይቆጠቡ ግምት ውስጥ ባለበት ሁኔታ) ሁሉም ትዮጵያዊ  ግን ዘርን (ጎሳን) ከተመለከተ ስድብ ተጠብቆ ካልታገለ ያቺን የምንወዳትን ምሉዕ ኢትዮጵያን ማየት ከንቱ እንዳይሆን እፈራለሁ ።
ይህ ማለት ደግሞ ርምጃችንን ሊገታን እንዳይችል ኢህአዴግ እየሸሸበት ካለበት ሩጫው እንዳያርፍ በጨዋነት ትግሉን መደገፍ እንደሚገባ ለማሳሰብ ነው።
ትግሉ አሁን በአራቱም ማዕዘን ይሸታል ሽታውም በቅርቡ ወደ ጪስነት ይለወጣል በዚህ ውስጥ ግን አንድነትና መከባበር ከየትኛውም ጊዜና ከመቼውም በላይ ቁልፍ ሆኖ ሊታይ ይገባዋል።

ሌላው ቀደም ሲል በሃገራችን የነጻነት ታሪክ ውስጥ ለአንድነትና ለሃገሩ ፍትህ ሲል ራሱን መስዋዕት ያደረገን ጀግና ትውልድ ሁልጊዜም ልናስበውና ልናመሰግነው (ሬኮግናይዝ ) ልናደርገው ይገባል ኢትዮጵያ የረዥም ዘመናት ታሪክ ባለቤት እንደመሆኗ ወደፊት ከመራመዳችን በፊት ወደኋላ ዞር ብሎ ማየት ለምንረግጠው ስፍራ አስተማማኝ ሊያደርገን ይችላል ::
ስለዚህ ያንን እንደሻማ ቀልጦ ለሃገሩ የሞተ ያ ጀግና ትውልድ ምንጊዜም አክብሮት ሊቸረው  ይገባል !!!
አለበለዚያ አሁንም የምናደርገው ትግል ሙሉ ሊሆን አይችልምና ዲያስፖራ ሆይ ሰከን በል  ::

መ/ት ምንታምር
ከደሴ